በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን መስከረም 28 2012
Date
ቁጥር 1/63/12
Ref.No

ለጉምሩክ ኮሚሽን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መመሪያ ስለመላክ፤

የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 164/2012 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክን ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አዳነች አበቤ
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት

ገቢዎች ሚኒስቴር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

# የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 164/2012

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት * Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2 *

የገቢዎች ሚኒስቴር

መስከረም 2012 ዓ.ም

# የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብተው ስለሚወጡበት ሁኔታለመወሰን የወጣ መመሪያ

የአገራችን የቱሪዝም ኢንደስትሪ ለአገራችን የገጽታ ግንባታ እና ለኢኮኖሚው ሊያበረክት የሚችለውንአስተዋፅዖ ለማሳደግ እንዲቻል ለቱሪስት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ቱሪስቶችማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታበግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፣

ቱሪስቶች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥበሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግልጽና ወጥ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የገቢዎች ሚኒስቴርበጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 71 (1) እና 180 (2)መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የቱሪስት መገልገያ ዕቃዎች በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብተው ስለሚወጡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር161/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

   ለየቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ፦

   1/ "ቪዛ" ማለት ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ ሰዎች የሚሰጥ የቱሪስት ቪዛ ነው።

   2/ "የቱሪስት መገልገያ ዕቃ" ማለት ቱሪስቱ የሚገለገልበት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብቶ በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሶየሚወጣ ዕቃ ሲሆን ተሽከርካሪን ይጨምራል።

   3/ "ተሽከርካሪ" ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ሰውን ለማጓጓዝ የሚያገለግል ተሽከርካሪ ሲሆን ሞተር ሳይክልን፣ ብስክሌትን የሚያካትት ሲሆንየደረቅና የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪን አይጨምርም።

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

4/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት አግባብነት ባለው ማስረጃ የሚረጋገጥ ከባድ ህመም ወይም በህግ ቁጥጥር ሥር መዋል ወይም ከአገር እንዳይወጣ መታገድ ወይም ዕቃው የጠፋ መሆኑ ከተረጋገጠ ከነዚህ ጋር ተመሣሣይ የሆነና ቱሪስቱ እንዳይመለስ የሚያደርግ ማንኛውም ሌላ ሁኔታ ማለት ነው።

5/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እንደተሻሻለ ነው።

6/ "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ሲሆን የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል።

7/ ሌሎች ቃላቶችና ሐረጎች በአዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ቱሪስቶች በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ አስገብተው በሚያስወጧቸው ዕቃዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታ</u>

ማንኛውም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ቱሪስት ከዚህ በታች የተመለከተቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል።

1/ ፓስፖርት፣

2/ የቱሪስት ቪዛ፣

3/ ቪዛ የማይሰጥበት ሀገር ከሆነ ከኢትዮጵያ ኢምግሬሽን የሚሰጥ የይለፍ ወይም መግቢያፈቃድ፣

4/ ተሽከርካሪ ይዞ የሚገባ ከሆነ ከመጣበት አገር ተሽከርካሪው ከአገርእንዲወጣ የተፈቀደበትማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቱሪስቱ መብትና ግዴታ</u>

5. <u>መብት</u>

ማንኛውም ቱሪስት፡-

(ሀ) ተሽከርካሪን ጨምሮ የቱሪስት ዕቃዎችን በጊዜያዊነት ማስገባት ይችላል።

(ለ) በዚህ አንቀጽ ፊደል (ረ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለጉዞ የሚያስፈልጉ የፍጆታ ዕቃዎችና ሌሎች መጠቀሚያዎችን ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ ይዞ መግባት ይችላል።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

(ሐ) የተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት የማራዘሚያ ጊዜ ለደንበኞችትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በማቅረብ ሲፈቀድ በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃዎችን አገር ውስጥ ማቆየት ይችላል፡፡

(መ) በዚህ አንቀጽ ፊደል (ሐ) መሰረት የሚደረገው የጊዜ ማራዘሚያ በአንድ ጊዜ ለሶስት ወር ይሆናል፡፡

(ሠ) በዚህ አንቀጽ ፊደል (መ) የተመለከተው ቢኖርም ለቱሪስቱ የሚሰጠው የጊዜ ማራዘሚያ በሀገር ውስጥ እንዲቆይ በሚመለከተው አካል ከተፈቀደው ጊዜ ሊበልጥ አይችልም፡፡

(ረ) ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ሰንጠረዥ የተዘረዘሩትን ዕቃዎችን ወደ አገርማስገባት ይችላል፣

(ሰ) ኮሚሽነሩ በልዩ ሁኔታ ሲፈቀድ በዚህ አንቀጽ ፊደል (ረ)በተመለከተው ሠነጠረዥ ያልተሸፈኑ ዕቃዎችን ይዞ መግባት ይችላል፡፡

(ሸ) በጊዜያዊነት ያስገባውን ዕቃ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ምክንያት መልሶ ማስወጣት ያልቻለ እንደሆነ ይህንኑ ለኮሚሽኑ በማሳወቅ ተሽከርካሪው ተመልሶ እስከሚወጣ ድረስ በአገሩ ኢምባሲ.ቅጥር ግቢ ወይም በጉምሩክ በተፈቀደ ቦታ ውስጥ ማቆየት ይችላል፡፡

(ቀ) ለተሽከርካሪው የሚያስፈልግ መለዋወጫ በአገር ውስጥ የማያገኝ ኮሆነ በቆይታ ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በማቅረብ ሲፈቀድለት ከቀረጥ ነፃ መለዋወጫውን ከውጭ አገር ማስመጣት ይችላል፡፡

6. <u>ግዴታ</u>

ማንኛውም ቱሪስት፡-

(ሀ) ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባውን ተሽከርካሪኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረትበዋስትና ማስመዝገብ አለበት፡፡

(ለ) ፕሮፌሽናል ካሜራ ይዞ የሚገባ ከሆነ ከመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት የተሰጠ ፈቃድ ማቅረብ አለበት፡፡

(ሐ) በጊዜያዊነትየሚያስገባቸውንዕቃዎችወደአገርማስገባትወይምከአገርማስወጣትያለበት በራሱ ብቻ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የመዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation N. 2

(መ) ተመልሶ የሚወጣበትን ጣቢያ መቀየር ያስፈለገው እንደሆነ አስቀድሞ ለጉምሩክ ኮሚሽን የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

(ሠ) በመግቢያ በሮች የመግቢያ ፈቃድ በመጠየቅ የተሽከርካሪ ዲክለራሲዮን መሙላት ያለበት ሲሆንዕቃው የተመዘገበበትን የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በሚዘዋወርበት ቦታ ሁሉ ይዞ የመገኘት እና ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

(ረ) የተፈቀደው የቆይታ ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር ዕቃውን የተፈቀደለት የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ መልሶ ከአገር ማስወጣት አለበት፡፡

(ሰ) ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ተመልሶ የሚወጣበት በር ለጉምሩክ መግቢያ በር ማሳወቅ አለበት፡፡

(ሸ) በአገር ውስጥ የቆይታ ጊዜ በተሽከርካሪው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ ፓሊስ ጣቢያ ወይም ለጉምሩክ ጣቢያ ወይም የአስተዳደር ጽ/ቤት ሪፓርት በማድረግ የፅሁፍ ማስረጃ ለጉምሩክቅ/ጽ/ቤት ወይም ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

(ቀ) ከአገር ተመልሶ ሲወጣ በመውጫ በርበሚገኝ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በመቅረብ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነ ስርዓት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

(በ) ማንኛውም በአገሪቱ ህግወይም አገሪቷ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ክልከላ የተደረገባቸውን ዕቃዎች ይዞ ወደ አገር ውስጥ መግባት አይችልም፡፡

(ተ) ወደ አገር ውስጥ ይዞት የሚገባው ዕቃ ገደብየተደረገበት የሆነ እንደሆነ ከሚመለከተውተቆጣጣሪ መ/ቤት ፈቃድ ማቅረብ አለበት፡፡

(ቸ) በዚህ አንቀጽ ፊደል (ሠ) መሠረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ሲሞላ ከተሽከርካሪው አገልግሎት ተያያዥነት ያላቸው እንደመለዋወጫ፣ማስጌጫ፣ቅያሬ ጎማ፣ የነዳጅ መያዣና ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች ጭምር በዲክላራሲዮን መመዝገብ አለባቸው፡፡

7. <u>ቱሪስቱ በጊዜያዊነት ያስገባቸውን ዕቃዎች ስለመወርስ</u>

1/ ማንኛውም ቱሪስት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ተሽከርካሪ ወይም ፕሮፌሽናል ካሜራ በህግ በተወሰነው ወይም በተሰጠ የማራዘሚያ ጊዜ ውስጥከአገር ያላስወጣ እንደሆነ ተወርሶ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ቱሪስቱ ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ተሽከርካሪ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት መውጣት ባለበት ጊዜ ውስጥ ተመልሶ



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation N.2

ከአገር የማይወጣ ከሆነ ተሽከርካሪው ተመልሶ ከአገር እስኪወጣ ድረስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 (ሸ) መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ አገር ውስጥ እንዲቀይ ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ተሽከርካሪው ሙሉ በሙሉ ጉዳት ደርሶበት ከአገር መውጣት የማይችል ካልሆነ በስተቀር በህግ የተመለከተው ወይም በኮሚሽኑ የተፈቀደለት የመቆያ ጊዜ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከአገር መውጣት አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተመልሶ ከአገር ያልጣ ተሽከርካሪ ተወርሶ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

5/ በዚህ መመሪያ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው ቢኖርም ቱሪስቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ያገኘ ከሆነ ወደ አገር ውስጥ ባስገባው ተሽከርካሪ ወይም ሌላ የግል መገልገያ ላይ የመኖሪያ ፈቃድ በተገኘበት ቀን ዕቃው ወደ አገር ውስጥ እንደገባ ተቆጥሮ የጉምሩክ ሥነ- ሥርዓት በመፈጸም ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

8. <u>ስለ መረጃ አያያዝ</u>

1/ ማንኛው ቱሪስት ወደ አገር ውስጥ በሚገባበትና በሚወጣበት በር ላይ የሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ አገር ውስጥ ስለሚገባውና ከአገር ውስጥ ስለሚወጣው ቱሪስትና ከቱሪስቱ ጋር ስለሚገቡና ስለሚወጡ ዕቃዎች የተደራጀ መረጃ መያዝ አለባቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተደራጅቶ የተያዘው መረጃ በየሣምንቱ ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እዲሁም በመረጃው ለሚጠቀሙ ሌሎች የሥራ ክፍሎች መተላለፍ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያዘውና የሚተላለፈው መረጃ በመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓትየተደገፈ መሆን አለበት፡፡

9. <u>ስለህግ ማስከበር</u>

ወደ አገር ውስጥ የገባ ቱሪስት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው ወይም የመቆያጊዜው ካልተራዘመለት በስተቀር በህግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ከአገር ያላስወጣ እንደሆነ የኢንተሊጀንስና ኮንትሮባንድ መካላከል ዳይሬክቶሬትና የቅ/ጽ/ቤት የህግ ተገዥነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ዕቃው ተይዞ ውርስ እንዲደረግና እንዲወገድ ይወስናል፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. **የተሻሩህጐች**

1/ ለቱሪዝምና ለባህል ልውውጥ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 116/2008 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሠራር በዚህ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

14. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መስከረም 21 ቀን 2012ዓ.ም.

አዳነች አቤቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2